

## ❧48-1☙

# ጠቃሚ ምክር
# “ከሰው ጋር መጋጨት ስለቸኝ” ለሚሉ

***“በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ ከየት የመጣ ነው? በሰውነታችሁ ውስጥ ከሚዋጋው ከሥጋዊ ምኞታችሁ አይደለምን?”***
(ያዕቆብ 4፥1)

ግጭት 1

ኤፍሬም ከጸሎት ስብሰባ በኋላ ልቡ በደስታ ተሞልቶ አጠገቡ የነበረውን ምናሴን እቅፍ አድርጎ “በጣም እወድሃለሁ” አለው። ምናሴ የኤፍሬምን ፍቅር በመቀበል ፈንታ “በጣም እወድሃለሁ” ያለው አነጋገሩ ልዩ ትርጉም ይዞ እንዲገባው ስለሆነ በጣም ተናደደ። “አሁን እወድሃለሁ የሚለኝ ከዚህ በፊት ይጠላኝ ነበር እንዴ!” በማለት ልቡ ከዚያን ቀን ጀምሮ በምናሴ ላይ ቅሬታና ቂም አዘለ። ኤፍሬምን የሚጎዳበት መንገድ ቢያገኝ ከመጉዳት ወደ ኋላ አይልም ነበር።

ግጭት 2

ደበበ መኪናው ውስጥ ገብቶ የመኪናውን ጥሩምባ (ክላክሱን) እየደጋገመ በኃይል ያስጮሃል። “መጀመሪያ በሩን ከፍተህ መኪና ውስጥ ስተገባ ሰምቼሃለሁ፤ ይህን ያህል የአካባቢውን ጸጥታ እስከትነሳ ድረስ ክላክስ የምታስጮኸው ደንቆሮ መስየሃለሁ እንዴ!” አለችው በመቆጣት ባለቤቱ ዙሪያሽ ወርቅ። “መቼ ነው አንቺ ሰዓት የምታከብሪውና በጊዜ ተነስተሽ የምንፈልግበት ቦታ መሄድ የምንችለው?” “ሰዓት አክባሪ ሆነህ ልብህ ወልቁኣል፤ መቼ ነው አንተ ደግሞ ሳትጨቃጨቅ በሰላም የምትውለው?” “ሰዓት ብታከብሪ እኮ ምንም ባልተናገርኩሽ ነበር!” “እኔ እኮ እንደ አንተ ወንድ አይደለሁም፤ ሴት ነኝ። ራሴን ብቻ ሳይሆን ልጆቼንም ማልበስ አለብኝ” አለችው። በዚህ ዓይነት እየተጨቃጨቁ ቤተ ክርስትያን ደርሱ። “በዚህ ዓይነት መንፈስ ቤተ ክርስትያን ገብተን ምን ዓይነት በረከት ልናገኝ ነው?” ስትል ዙሪያሽ ወርቅ ጠየቅአቸው። ደበበም “የጥል መነሻ መፍረስ እንደ ጀመረ ግድብ ነው፤ ስለዚህ ጥል ከማስከተሉ በፊት ክርክርን አቁም” (ምሳሌ 17፥14) የሚለው ቃል ትዝ ሲለው ንግግሩን አቆመና፡- “ይቅርታ! የእኔ ጥፋት ነው። የፈለግሽውን ያህል ጊዜ ብታሳልፊም ዝም ማለት ነበረብኝ። ሁለተኛ አፌን እቆልፋለሁ” አላትና ወደ ቤተክርስትያን ገቡ።

ግጭት 3

የሰለሞን አለቃ ሥራውን ያገኘው በቂ ትምህርትና የሥራ ልምምድ ኖሮት ሳይሆን በዘመድ ስለነበረ በትምህርቱና በሥራ ልምምዱ የተሻለ አቋም ያለው ሰለሞን ስልጣኔን ይወስድብኝ ይሆናል በማለት ፍርሃት ስለነበረው ሰለሞን ተበሳጭቶ ሥራውን ለቅቆ እንዲሄድ በተለያየ መንገድ ይተናኮለዋል። በአለቃው የተበሳጨው ሰለሞንም ራሱን እየነጨ “አሁንስ ሰለቸኝ፤ ተንስቼ ሌላ ሥራ መፈለግ አለብኝ። በዚህ ዓይነት ጭንቀትና ግፊት ባለበት ሁኔታ ከአለቃዬ ጋር ተስማምቼ ሠርቼ መኖር አልችልም። ሥራዬን በጣም እወደው ነበር፤ ግን አለቃዬ ነፍሴን ሊያወጣት ነው። የምሠራው ሥራ ፈጽሞ አይጥመውም፤ አንድ ቀን ሥራህ ጥሩ ነው ብሎኝ አያውቅም። በዚህ ላይ ደግሞ የሚሰጠኝ ትዕዛዝ ፈጽሞ የማይጨበጥ ነው፤ በየጊዜው ሀሳቡን ይለዋውጣል። ስለማይወደኝ ሥራውን ትቼ እንድሄድ ይገፋፋኛል። አሁንስ ከእርሱ ጋር መጋጨቱ ሰለቸኝ። በውስጤ የሚሰማኝን ብነግረው ከሥራዬ ያባርረኛል። ከዚህ ወጥቼ ደግሞ ሌላ ሥራ ማግኘት አልችልም” አለ።

ከላይ ሦስት ዓይነት ግጭቶችን በምሳሌ አይተናል። አንደኛው በኤፍሬምና በምናሴ መካከል የተፈጠረው ግጭት ነው። “አሁን እወድሃለሁ የሚለኝ ከዚህ በፊት ባይወደኝ ነው” የሚለው ትርጉም የእርሱ ትርጉም እንጂ የኤፍሬም ትርጉም አልነበረም። ምናሴ የኤፍሬምን መንፈስ በትክክል ስላልተረዳለት ከዚያን ቀን ጀምሮ ኤፍሬም የሚሠራው የማይጥመው፣ የሚናገረው የማይጣፍጠው ሆነ። ምናሴ ኤፍሬምን የጠላው መንፈሱን በትክክል ስላልተረዳለት ብቻ እንጂ፥ ኤፍሬም ምናሴን በድሎት ወይንም ጎድቶት አይደለም።

ሁለተኛው ዓይነት ግጭት በባልና በሚስቱ መካከል የተፈጠረው ግጭት ነው። የግጭታቸው ምክንያት ሚስትዬዋ በሰዓቱ ተነስታ ከቤት መውጣት ባለመቻሏ ይመስላል። ይሁን እንጂ በምን ምክንያት እንደምትዘገይ ባሏ የተረዳላት አይመስልም። እርሷም ችግሯን ገልጻ ዕርዳታ የምትፈልግ መሆኗን መናገሯ ያጠራጥረናል። እርሷ ልጆቿን ለማልበስ ስትታገል እርሱ መኪና ውስጥ ገብቶ መቀመጡ ይበልጥ ያበሳጫታል። ሁልጊዜ በዚህ ምክንያት ይጣላሉ። እርሱም “መዘግየት ልማዷ ነው” እርሷም “መጨቃጨቅ አመሉ ነው” ማለት ብቻ ችግሩን አያቃልለውም። ወይንም ደበበ “ሁለተኛ አልናገርሽም! የፈለግሽውን ያህል ጊዜም ብትወስጂ ዝም እላለሁ” ማለቱ ብቻ አሁንም ችግሩን አይፈታውም። ዙሪያሽ ወርቅና ደበበ ቁጭ ብለው በጥሞና መነጋገር ያስፈልጋቸዋል። ዙሪያሽ ወርቅ ባሏ መኪና ውስጥ ቁጭ ብሎ በመጠበቅ ፈንታ ልጆቹን በማልበስ እንዲረዳት ልትነግረው ይገባል። ደበበም ልጆቹን ማልበስ የሴት ሥራ  (ሀላፊነት) ነው በማለት ለብቻዋ ስትታገል ማየት የለበትም። በአጠቃላይ ችግሩ የሚቃለልበትን መንገድ ተወያይተው የተሻለ ዘዴ መፈለግ ይኖርባቸዋል። አለበለዚያ ውስጣቸው እያረረና እየደበነ ስለሆነ ጤንነታቸውን ያጓደላሉ፤ ፍቅራቸውን ይሻክራል።

ሦስተኛ ግጭት ሰለሞን ከአለቃው ጋር ያለው ግጭት ነው። ከአለቃው ጋር ያለው አለመግባባት መፍትሄ ሊገኝለት የሚችለው ሰለሞን የሚሰማውን በመግለጽ ከአለቃው ጋር መነጋገር የቻለ እንደሆነ ብቻ ነው። የእግዚአብሔርም ቃል ይህንን እንዲያደርግ ይመክረዋል። “በአንተና በባልንጀራህ መከከል አለመግባባት ቢፈጠር ከእርሱ ጋር ብቻ ተወያይተህ አለመግባባትህን አስወግድ…” ይላል (ምሳሌ 25፥9)። የሰለሞን አለቃ በፍርሃትና በጥርጣሬ ስለተሞላ መነጋገሩ ብቻ ችግሩን ሊያቃልለው አይችልም ይሆናል። ቢሆንም ለሰላም በር ይከፍታል።

ሦስት ዓይነት ዋና ዋና ግጭቶች አሉ፡-
ሀ) በትክክል ባለመረዳት (misunderstanding) ምክንያት የሚፈጠር ግጭት
ለ) በጥላቻ ምክንያት የሚፈጠር ግጭት
ሐ) ጥላቻ ሳይኖር እንዲሁ የሚፈጠር ግጭት

ሀ. በትክክል ባለመረዳት (misunderstanding) ምክንያት የሚፈጠር ግጭት

ሰዎች ሀሳባችንን በትክክል ባለምረዳታቸው ምክንያት ብቻ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ልንጋጭ እንችላለን። ሁላችንም በዚህ ዓይነት ልምምድ ውስጥ ስላለፍን ሀሳቡ ይህን ያህል አዲስ አይሆንብንም። ድርጊታችንን ወይንም መንፈሳችንን በትክክል ላልተርዱልን ወይንም በተሳሳተ መልክ ለገባቸው አንዳንድ ሰዎች ባለን ኃይልና ጥበብ ራሳችንን ለመግለጽ ብንሞክርም “ተሳስቻለሁ፣ መስሎኝ ነበር፣ አዝናለሁ!” ላይሉን ይችላሉ። እንዲያውም መልካሙ ተግባራችን መጠላትና መሰደድን ሊያስከትልብን ይችላል። ይህ እንዲህ ሆኖ ብናየው መንፈሳችንን አይጭነቀው፤ ልባችን አይሰበር። ምክንያቱም ያለዚያ ሙሉ  በሙሉ በሕይወታችን ማደግ አንችልም። እዚህ ላይ አንድ የሚያጽናና ነገር አለ። ይኸውም የጥንት መንፈሳዊ አባቶቻችንም በዚህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ ያለፉ መሆናቸውን ማወቁ ነው። አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሯቸው ሁኔታን በቀጥታና እንዳለ መመልከት ስለማይሆንላቸው ነገርን በልባቸው ቋጥረው ማንኛውንም ነገር አጨልመው የሚያዩና ወደ ግራ የሚያነቡ ናቸው። አንድ ጊዜ ነገር ከነከሱ አይለቁም። በአካባቢያችን ይህን ዓይነት የተፈጥሮ ባህሪ ያላቸው አንዳንድ ሰዎች ቢያጋጥሙን ራሳችንን መርምረን ህሊናችን ንጹህ ከሆነ የእነርሱ እኛን መጥላት እንዲያስበረግገን፣ ዓላማችንን እንዲያጨልምብን፣ ሰላማችንን እንዲገፍብን መፍቀድ የለብንም። የእኛ ሥራ፣ የእኛ ንግግር እነርሱን ባይጥማቸውና ባይጣፍጣቸው የእኛ ሕይወት በእነርሱ አስተያየትና ግምት ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ ሌሎች የሚወዱንና የሚፍልጉን እንደሚኖሩ በመረዳት ያለሥጋት ወደ ፊት እንቀጥል።

ለ. በጥላቻ ምክንያት የሚፈጠር ግጭት

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጥላቻ ምክንያት ግጭት ከደረሰባቸው ሰዎች መካከል አንደኛው ዳዊት ነው። ዳዊት የእሥራኤል የሚቀጥለው ንጉሥ እንዲሆን በነብዩ በሳሙኤል ሲቀባ (1ኛ ሳሙኤል 16፥13) ከእሴይ ቤተሰብ በስተቀር በሕዝቡ የታወቀ አልነበረም። እግዚአብሔር ለከፍተኛ ዓላማ የሚመርጣቸውን ሰዎች አስቀድመው በልዩ ልዩ ችግርና መከራ ውስጥ እንዲያልፉ የደርግ ነበር። ዳዊትም ከዚህ ነጻ አልነበረም። በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ በሕዝቡ ላይ ከመንገሡ በፊት በሸካራው መንገድ ማለፍ ስለነበረበት የሚጠሉት ሰዎች በተለያየ ምክንያት በሚያደርሱበት ጉዳት  ውስጥ በማለፍ ጠቃሚ የሕይወትን ትምህርት ማግኘት ቻለ። ሰዎች በተለያየ ምክንያት ጠልተውን ሊጎዱን ሲሞክሩ ስናይ ዳዊት ያለፈበትን ሕይወት እያስታወስን እንጽናና። በዚያ ውስጥም አልፈን ሰፊ የሕይወት ልምምድ እንዲኖረን እግዚአብሔር ፈቅዶ ይሆናል በማለት በደስታ መቀበልም እንዳለብን አንርሳ።

ዳዊት የእሥራኤል ሠራዊት በተዋረደበትና ባፈረበት ሰዓት ደርሶ ፍልስጤማውያንን የመታ ሰው ነው (1ኛ ሳሙኤል 17)። ባገኘው ድል ሴቶች በዘፈንና በጭፈራ ተቀበሉት። “ዳዊት ጎልያድን ገድሎ ሲመለስና ወታደሮችም ወደየቤታቸው በማምራት ላይ ሳሉ በእሥራኤል በሚገኙ ከተሞች ሁሉ የሚኖሩ ሴቶች ሳኦልን ለመቀበል ወጡ፤ እነርሱም በእልልታ እየዘፈኑና እየጨፈሩ፥ የመሰንቆ ድምጽ እያሰሙ አታሞ ይመቱ ነበር። ሴቶቹም ባደረጉት አቀባበል ሥርዓት ላይ ‘ሳኦል ሺ ገዳይ! ዳዊት ግን አሥር ሺ ገዳይ!’ እያሉ አሞገሡ” (1ኛ ሳሙኤል 18፥6-7)። የሴቶቹ ዘፈን ንጉሥ ሳኦል ስለረበሸውና በጣም ስላልስቆጣው እንዲህ አለ “ዳዊትን አሥር ሺ ገዳይ! ብለው ሲያሞግሱ እኔን ግን ሺ ብቻ ገዳይ! አሉኝ። በዚህ ዓይነት ከሆነማ ወደፊት እርሱን ሊያነግሱት ነው!” አለ (1ኛ ሳሙኤል 18፥8)። ይሄ ሳኦልን በጣም ስላስቆጣው “ከዚያን ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ ቅንአትና ጥርጣሬ አደረበት” ይላል 1ኛ ሳሙኤል 18፥9።

እዚህ ላይ የዳዊትን በደል አናይም። ይሁን እንጂ ሳኦል “ዳዊት ዙፋኔን ሊነጥቅ የመጣ ሰው ነው” ሲል ሳኦል ስለ ዳዊት ትክክለኛ ግምት እንዳልነበረው እንረዳለን። ዳዊት በእግዚአብሔር መለኮታዊ ምሪትና ፈቃድ ሆኖ ጎልያድን መምታት ቻለ እንጂ የንጉሥነቱን ዙፋን ፈልጎ አልነበረም። የሳኦል ችግር ለራሱ የተመኘውን ክብር ዳዊት የወሰደበት መስሎ ስለተሰማው ነበር። በመሠረቱ የንጉሥነቱን ስልጣን ለማን እንደሚሰጥ ወሳኙ እግዚአብሔር እንጂ ዳዊት ወይንም ዘፋኞቹ ሴቶች እንዳልሆኑ ቢረዳ ኖሮስ ሳኦል እግዚአብሔርን እንጂ ዳዊትን ወይንም አሞጋሾቹን መፍራት ባልተገባውም ነበር።

በራሱ ችሎታና ዕውቀት የማይተማመን ሰው በአካባቢው ከእርሱ የተሻለ ሰው ያለ ሲመስለው በፍርሃትና በስጋት የሚያደርገውን መወራጨት የሚያውቅ ሰው ሳኦል በዳዊት አካባቢ ሲሆን ይሰማው የነበረውን ስሜት መረዳት ይህን ያህል አያስቸግረውም። ሳኦል ዳዊትን ቢጠላውና ሊገድለው ቢሞክር ይህን ያህል አይገርመንም። ምክንያቱም ቅንአት ሰውን በጥላቻ የሚሞላ መሆኑን ስለምናውቅ ነው። “ቁጣ በጭካኔና በጥፋት የተሞላ ነው፤ ቅንአት ግን ከቁጣ የባሰ ነው” ይላል (ምሳሌ 27፥4)። ትንሿ የዳዊት እንቅስቃሴ በሳኦል ሕይወት ውስጥ ትልቅ ስጋትና ፍርሃትን ይጨምር ነበር። በቅንአት ተሞልቶ አዕምሮውን አጥቶ እንደ አውሬ ከሚያድነው ከሳኦል ለመዳን የግድ መሸሽ ነበረበት። ለዚህ ነው ዳዊት ብዙ ዘመኑን በሽሽት እንዲያሳልፍ የሆነው። በዘመናችንም ብዙ ሳኦልን የሚመስሉ ሰዎች አሉ። ከእነርሱ ጋር ተቀራርቦና ተስማምቶ መኖር የማይቻል በመሆኑ መሸሽም የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ከእንደዚህ ዓይነት ባህርያቸው ጠማማ ከሆነ ሰዎች (Irregular People) ጋር ለመኖር አለመቻላችን ችግሩ የእኛ ሳይሆን በእነርሱ በኩል ስለሆነ “ግጭቱ በዛብኝ፤ ከበደብኝ” ብለን ልናማርር አይገባም።

ዳዊት አጥፊው ከነበረው ከሳኦል ፊት ሸሸ እንጂ እንደ አመጣጡ ልመልስለት ብሎ ምንም ዓይነት የበቀል እርምጃ እንዳልወሰደ እናውቃለን። ዳዊት “ሰውን ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ ወደድ እንጂ በማንም ላይ በቀል አትፈጽም፤ ቂምም አትያዝ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ” (ዘሌዋውያን 19፥18) የሚለውን ትዕዛዝ በሕይወቱ የሚለማመድ ሰው ነበር። ዳዊት ጠላቱን ሳኦልን መትቶ የሚጥልበት ዕድል በተደጋጋሚ አግኝቶ በእርሱ ላይ ሳይፉን ከመምዘዝ ይልቅ መሸሽን መረጠ። እኛም ባህሪያቸው ጠማማ በሆኑ ሰዎች (Irregular People) በተደጋጋሚ ተወግተን ከምንቆስል መበቀሉን ለእግዚአብሔር ትተን መሸሹ አዋቂነት ይመስለናል። ብዙ መጽሀፍ ቅዱስ አዋቂዎች መዝሙር ምዕራፍ 140 ዳዊት ከሳኦል በሚሸሽበት ጊዜ የዘመረው መዝሙር እንደነበረ ይናገራሉ። ይሄ መዝሙር በጥላቻ ልባቸው የተሞላ ሰዎች በሌላው ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ክፉ ነገሮች ይገልጻል።

..........................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**